# ቅንጅት ባካሄደው የስም ለውጥ ላይ ከአባላቱ ጋር ውይይት አደረገ

በክቡር ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል የሚመራው፣ መስከረም 14 ቀን 1998 ዓ.ም የተዋሃደው ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ስሙን በመለወጥ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ተብሎ ለመጠራት መወሰኑን ነሐሴ 25 ቀን 2000 ዓ.ም በፓርቲው ዋና ጽ/ቤት በተጠራ የአባላት ስብሰባ ላይ አስታውቋል።

ይህንኑ ቅንጅት ስሙን መለወጡን ያስታወቀበትን ስብሰባ የፓርቲው የሥራ አስፈጻሚ ኰሚቴ በጋራ የመራው ሲሆን በዕለቱ አቶ አባይነህ ብርሃኑ የፓርቲው ምክትል





ፕሬዚዳንት፣ አቶ ወንድወሰን ተሾመ ዋና ጸሐፊ፣ ወ/ሮ ዓለሚየሁ ሞገድ የሴቶች ጉዳይ ኰሚቴ ኃላፊ፣ አቶ አባተ ተገኝ የማኅበራዊ ጉዳይ ዘርፍ ኃላፊ፣ እንዲሁም ወጣት ጌታቸው አበበ እና አቶ ተስፋዬ ታሪኩ የሥራ አስፈጻሚ ኰሚቴ አባላት፤ ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲን ለማዳን የተከፈለውን መስዋዕትነት እንዲሁም የኢትዮጵያ ሕዝብ ያጣውን የሕግ የበላይነት ለማምጣት ፓርቲው የሚጠብቀውን ከፍተኛ ትግል በማስመልከት በየተራ ሰፊ ገለጻ አድርገዋል።

በዕለቱ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴን በመወከል በቴዎድሮስ አደባባይ አካባቢ በሚገኘው በፓርቲው ጽሕፈት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ለተሰበሰቡት ለፓርቲው አባላትና ደጋፊዎች የቅንጅት ስም መለወጡን ያስታወቁት ወይዘሪት መሶበወርቅ ቅጣው የፓርቲው የሕዝብ ግንኙነት ጉዳይ ኃላፊ ናቸው።

ወ/ሪት መሶበወርቅ ቅጣው በዚህ ወቅት ባሰሙት ንግግር ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ከጥምረቱ አንስቶ እስከ ዛሬ ለሕዝቡ ነፃነት፤ ለሰላም፤ ለፍትሕ እንዲሁም ለዴሞክራሲ በተከታታይ የከፈለውን መስዋዕትነት በዝርዝር አስታውሰዋል። አያይዘውም ቅንጅት የሚለው ስያሜ ለሌላ አዲስ ለተፈጠረ ድርጅት መሰጡትን በማስመልከት ሲናገሩ <<… በምርጫ 97 ቅስቀሳ ያካሄድንበትን፤ የተወዳደርንበትን፤

ለአምስት ዓመታት የተመረጥንበትን፤ የታሠርንበትን፤ የተከሰስንበትንና ሌሎችንም መስዋዕትነቶችን ሁሉ የከፈልንበትን ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ የተሰኘውን ስማችንን ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ለሌላ አካል ስለሰጠብን አምርረን ተቃውመናል>> ብለዋል።





ሰኔ 14 እና 15 ቀን 2000 ዓ.ም የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ጠቅላላ ጉባዔ መካሄዱን ያስታወሱት ወ/ሪት መሶበወርቅ ቅጣው በማያያዝ ደግሞ ያሁኑን የፓርቲውን ስም ለመምረጥ የተደረጉትን ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች ሲያብራሩ <<እኛ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትም ጠቅላላ ጉባዔው የሰጠንን ኃላፊነት መሠረት በማድረግ የስም ለውጥ ለማድረግ መንቀሳቀስ ጀመርን። በዚህም መሠረት በአገር ውስጥና በውጭ የሚኖሩ አባላትና ደጋፊዎች በቀጥታ ስም በማውጣቱ ሂደት እንዲሳተፉ ጥሪ አቀረብን። በመሆኑም ከ70 በላይ ስሞች ከተለያዩ ሥፍራዎች ወደ ዋናው የፓርቲው ጽ/ቤት ተላኩ። ከተላኩት አማራጭ ስሞች መካከል <<የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት>> የሚለው የፓርቲ ስያሜ በአባላትና በደጋፊዎች በከፍተኛ ድምፅ ድጋፍ ያገኘ መሆኑን ወደ ፓርቲው ከመጡት የስያሜ ሰነዶች ለመረዳት ተችሏል። የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴውም እንደዚሁ በሙሉ ድምፅ ሊመረጠው ችሏል>> በማለት አስረድተዋል።

አቶ የወንድወሰን ተሾመ በበኩላቸው አዲሱን የፓርቲውን ስያሜ ለመምረጥ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ጊዜያዊ የአማራጭ ስሞች አጣሪ ኮሚቴ በማቋቋምና የመምረጫ መመዘኛዎችን በማዘጋጀት ሥራውን በከፍተኛ ጥንቃቄና በኃላፊነት ስሜት መከናወኑን በማስረዳት ገለጻ አድርገዋል።

እንዲሁም አቶ አባይነህ ብርሃኑ ከስብሰባው ተሳታፊዎች ለተነሱ በርካታ ጥያቄዎች ተገቢውን መልሽ ሰጥተዋል።

በዕለቱ ወደ 350 የሚጠጉ አባላትና ደጋፊዎች በስብሰባው ላይ የተገኙ ሲሆን ጠንካራ የድጋፍ አስተያየቶች ሲሰጡ ቆይተው ባንድ ድምፅ **የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት** የሚለውን ስያሜ መቀበላቸውን አረጋግጠዋል።